# እግዜርም እንደ ሰው ሆነብን ዘንድሮ(አዳነ መኮነን)

እግዜርም እንደ ሰው ሆነብን ዘንድሮ

ብንጮህ ወደ እርሱ ብናሰማ እሮሮ

አልሰማነም እግዜር ከኛ ተሰውሮ

የሰው ልጅ አለቀ በሦስት ነገር አርሮ።

ምን በድለን ይሆን ከዓለም የተለየ

ምን ኃጢአት ሰርተን ይሆን ከህዝብ የተለየ

ፊቱን ከእኛ  ያዞረ እንባችን እያየ።

መከራው በዛብን በሀገር በስደት

በአንድላይ ሰብስበው አጎሩን እንደ ከብት

አስረው ደበደቡን የፍጢኝ የኋሊት

ገለው እሬሳችን ጎተቱ በመሬት

ሰዎች ሳይሆኑስ የዲያብሎስ ሰራዊት።

ሰው መሆናችን ቀርቶ ልክ እንደ እንስሳት

አሳንሰው  አዩን  ከውሻ  ከድመት።

ስምም አወጡልን ያ ሃይዋን ከልብ ብለው

የበንዚሉ ሽታ ናላቸውን ያዞረው።

ዜጎቹ የሚለን መንግሥት ስለሌለን

በአራቱ ማእዘን በዓለም ተበትነን

መከራው በዛብን ስቃያችን አየን።

ባለቤት የጠላውን አሞሌ ባለዳ አይቀበለው

ያ  የድሮ  ተረት  የሚሉት  አበው

አሁን በእኛ ላይ ደርሶ ሲፈጸም  አየነው።

አምላክም  እንደ ሰው ሆነብን ዘንድሮ

ወደ እሱ ብናለቅስ ብናሰማ እሮሮ

አላየነም እሱ ፊቱን ከእኛ አዞሮ።

እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም ስንገላታ

ፍርድህን ስጥ እንጂ እንድናገኝ እፎይታ

የኃያላን ኃያል፤ የንጉሦች ንጉሥ የሰማዩ ጌታ።

ህዳር ፡፲፪ ቀን፤ ፪ሺ፲፫ (21/11/2013)